# አዎ ለምን ይሙት ድህ

(ከ አሊ ሁሴን)

ለምን አይዘገንን፣
　　　　እንዴት አያስከፋ፣
ድህ በሰልፍ ሲሞት፣
　　　　አይዞህ ባይ ሲጠፋ?

ዕድሜውን ተላብሶ፣
　　　በተፈጥሮ ታሞ፣
አይዞህ ባይ አግኝቶ፣
　　　ለመዳን ታክሞ::

ሰብዕናው ተከብሮ፣
　　　　ለመሞት ቢገደድ፣
ያማ! ተፈጥሮ ነው፣
　ይሂድ ይሰናበት እንጦርጦስ ይውረድ!

ግና!!
ሞፈርና ቀንበር፣
　　　ተሸክሞ ገፍቶ፣
ጉልበቱን ለግሶ፣
　　　ሌላው በሱ በልቶ፣
ከእንስሳ ባነሰ ፣
　ሀፍረተ ሥጋውን መሸፈኛ አጥቶ፣
በቁመና እያለ ክምሩን ሞት ሙቶ፣
ሣር ነጭቶ እየበላ፣
　　　ሆኖ ንብረት አልባ፣
ለምን ይሙት ድህ?
　　　እንዴት ገደል ይግባ?

ስንት ባንዳ እያለ፣
ስቃዩን አርዛሚ ፕሮፌሰር ዶክተር!
ለምን ይሙት ድህ!
አንዴም ሳያልፍለት ከጉድጓድ ይቀርቀር!?

ከአምባገነን ገዢው የካንሰር በሽታ፣
ሽሮ ሳያገግም ሳያገኝ እፎይታ፣
አይኖሩትን ኑሮ፣
ቆፍሮ ገብሮ፣
ፍዳ መከራ አይቶ፣
ወገን አስተምሮ፣
እህል ሳበደረ፣
ምሳሹ ሆኖ አፈር፣
ውስጡ አካሉ በግኖ፣
ከማፈር በስተቀር፣
ለምን አይታገል፣
ይታገላል ድሀ፣
የሚበላው የለ፣
የሚጠጣው ውሀ፣
ታገል ብሎ ጥሪ፣
ካልሆነ ለበጣ፣
ይታገላል እንጂ፣
ድሀ ምኑን ሊያጣ ፡፡
እኮ ምኑን ሊያጣ!
ከሞተ በኋላ ሊፀድቅ መች አስቦ፣
በሕይወት እያለ በችግር በስቃይ
ለሚያልቀው ተርቦ፡፡
ዓመቱን ጠብቆ በክረምት ወራት፣
ብጥቅጣቂ ጨርቁን ቅያሪ የሌላት፣
እላዩ ላይ አጥቦ ሳትወልቅ ለሚያሰጣት፣
ወይስ አስጎምጅቶት መንግሥተ ሰማያት?

ስንት ባንዳ እያለ፣
ስቃዩን አርዛሚ ፕሮፌሰር ዶክተር!
ለምን ይሙት ድሀ፣
አንዴም ሳያልፍለት፣ ከጉድጓድ ይቀርቀር?

ለምን አይዘገንን፣
እንዴት አያስከፋ፣
ድሀ በሰልፍ ሲሞት፣

**አይዞን ባይ ሲጠፋ!**